የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ
መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

በትግራይ ክልል ወደ ቀድሞ የመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲመለሱ የተደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ የተከናወነ የክትትል ሪፖርት

ሚያዝያ 2017 ዓ.ም.

www.ehrc.org

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በትግራይ ክልል ወደ ቀድሞ የመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲመለሱ የተደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ የተከናወነ የክትትል ሪፖርት

ሚያዝያ 2017 ዓ.ም.

መግቢያ

1. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት ምክንያት ተፈናቅለው በትግራይ ክልል የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በተመለከተ ክትትል ሲያከናውን የቆየ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም በክልሉ በሚገኙ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ዙሪያ የክትትል ሪፖርት የካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው። ኢሰመኮ ወደ ቀድሞ የመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲመለሱ የተደረጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ ለመረዳት ከነሐሴ 19 እስከ ጳጉሜን 1 ቀን 2016 ዓ.ም. በክልሉ ደቡባዊ ዞን እና ሰሜን ምዕራብ ዞን ክትትል አከናውኗል። በደቡባዊ ዞን ሥር ኮረም ከተማ፣ አፍላ ወረዳ፣ ሕጉም ቡርዳ እና ፋላ ቀበሌ፣ በራያ አላማጣ ወረዳ፣ ዋጃ ጡሙጋ ቀበሌ፣ በአላማጣ ከተማ፣ 02 እና 03 ቀበሌ እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ዞን ጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ በክትትሉ የተሸፈኑ አካባቢዎች ናቸው።

የክትትሉ ሥነ ዘዴ

2. ኢሰመኮ የክትትል ሥራውን ያካሄደው አግባብነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች እና ሰነዶችን በተለይም አህጉራዊ የሆነውን እና ኢትዮጵያ ያጸደቀችውን የአፍሪካ ኅብረት የሀገር ውስጥ የተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍ ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) መሠረት በማድረግ ነው።

3. በክትትሉ በቡድን ውይይት፣ በቃለ መጠይቅ፣ በሰነድ ምርመራ እና በአካል ምልከታ መረጃዎች እና ማስረጃዎች ተሰብስበዋል። ከተመላሾች ጋር ጸታን፣ ዕድሜን እና የአካል ጉዳት ሁኔታን መሠረት ያደረጉ 11 የቡድን ውይይቶች፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የመከላከያ ሰራዊት እንዲሁም የጤና ተቋማት ኃላፊዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ የተራድዖ ድርጅቶች የሥራ መሪዎች እና የሀገር ሽማግሌዎች ጋር 28 ቃለ መጠይቆች እና የተናጠል ውይይቶች ተደርገዋል። በተጨማሪም አግባብነት ያላቸው ሕጎችና ሰነዶች ምርመራ እንዲሁም ተመላሾች በሚገኙባቸው ጊዜያዊ ማቆያዎች የአካል ምልከታ ተከናውኗል። በተጨማሪም ኢሰመኮ ጎዳር 20 ቀን 2017 ዓ.ም. በመቐለ ከተማ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ አካሂዶ የነበረ ሲሆን በመድረኩ ከተገኙ የፌዴራል፣ የትግራይ ክልል እንዲሁም የደቡባዊ ዞን እና የሰሜን ምዕራብ ዞን የሥራ ኃላፊዎች ጋር በክትትሉ ቀዳሚ ግኝቶች እና ምክረ ሐሳቦች ዙሪያ ውይይት አከናውኖ ተጨማሪ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሪፖርቱን ለማዳበር ተችሏል።

4. ኢሰመኮ ይህንን ክትትል ሲያካሂድ የተጠቀመው የማስረጃ ምዘና ደረጃ በተመሳሳይ የክትትል ሥራዎች የሚጠቀመውን "ምክንያታዊ ጥርጣሬ" (reasonable suspicion) ተብሎ የሚታወቀውን የማስረጃ ምዘና መስፈርትን ሲሆን ይኸውም በአንድ ቀጥተኛ ከሆነ ምንጭ ተፈጸመ ወይም ደረሰ የተባለ ድርጊት ወይም የሰብአዊ መብት ጥሰት ቢያንስ በሌላ በአንድ ነጻ ወይም ገለልተኛ እና ተዓማኒ የሆነ ምንጭ ሲረጋገጥ ነው።

የመፈናቀል ዐውድ

5. ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. በህወሓት እና በፌዴራል መንግሥት መካከል በተቀሰቀሰው እንዲሁም ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም. ዳግም ባገረሸው የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ምክንያት ከ76 ሺህ በላይ ሰዎች ከሰሜን ምዕራብ ትግራይ አካባቢዎች በተለይም ከጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይጸብሪ ከተማ ተፈናቅለዋል። ተፈናቃዮቹ በሽረ፣ መቐለ፣ አክሱም፣ አድዋ፣ ዓብይዓዲ እና አዲግራት ከተሞች በሚገኙ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ተጠልለው የቆዩ ሲሆን፣ ከሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ከ56 ሺህ በላይ ተፈናቃዮች ወደ አካባቢያቸው ተመልሰዋል።

6. ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም. እንዲሁም ጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም. ዳግም በተቀሰቀሰው የሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከ52 ሺ በላይ ሰዎች ከአላማጣ፣ ኮረም፣ ኦፍላ፣ ራያ አላማጣ፣ ጨርጨር እና ዛታ አካባቢዎች ተፈናቅለዋል። ተፈናቃዮቹ በዋናነት በማይጨው፣ መሆኒ፣ መቐለ፣ ውቅሮ፣ አዲግራት፣ አክሱም እና ሽረ ከተሞች በሚገኙ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ለ1 ዓመት ከ7 ወር የቆዩ ሲሆን፣ ከሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ይህ ክትትል እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ 48,593 ተፈናቃዮች ወደ ቀድሞ የመኖሪያ አካባቢዎቻቸው ተመልሰዋል።

7. በዚህ ክትትል የተሸፈኑ አካባቢዎች ላይ የሲቪል አስተዳደር ባለመኖሩ ተፈናቃዮች ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው የተሟላ ዘላቂ መፍትሔ በሚያገኙበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

የሕግ ማዕቀፍ

8. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች እና በትጥቅ ግጭት ወቅት በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕጎች ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሀገር ውስጥ መፈናቀል ላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሠረታዊ መርሖዎች (“የተ.መ.ድ. መሠረታዊ መርሖዎች”) (UN Guiding Principles on Internal Displacement) እንዲሁም በአህጉር ደረጃ የካምፓላ ስምምነት በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መብቶች ጥበቃ ላይ ዝርዝር መርሖችንና ድንጋጌዎችን ይዘዋል።

9. ኢትዮጵያ የካምፓላ ስምምነትን በ2012 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 1187/2012 ያጸደቀች ሲሆን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የሀገሪቱ ሕግ አካል ነው። ስምምነቱ ሰዎችን ከሀገር ውስጥ መፈናቀል ለመጠበቅ፣ በመፈናቀል እንዲሁም በድኅረ መፈናቀል ወቅት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሊደረግላቸው የሚገባውን ጥበቃና ድጋፍ አስመልክቶ የአባል ሀገራትን እንዲሁም የታጠቁ ቡድኖችንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ግዴታዎች በዝርዝር ይደነግጋል።

10. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመፈናቀል ወቅት ለደረሰባቸው ጉዳት ተገቢውን ፍትሕ የማግኘትና እውነቱን የማወቅ መብትን ጨምሮ ዘላቂ መፍትሔዎችን የማግኘት መብት አላቸው። ወደ ቀድሞ የመኖሪያ ቦታቸው የመመለስ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ተዋሕዶ የመኖር ወይም ወደ ሌላ ቦታ የመስፈር የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች ሲሆኑ

ለዚህም መንግሥት ዘላቂነትን፣ የተፈናቃዮችን ደኅንነት እና ሰብአዊ ክብር እንዲሁም ፈቃደኝነት መሠረት አድርጎ ተጨባጭ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለበት። በተለይ በግጭት ዐውድ የተፈናቀሉ ሰዎችን ወደ ቀድሞ መኖሪያ አካባቢያቸው መመለስ እንደ አንድ ዘላቂ መፍትሔ የተወሰደ እንደሆነ ለመፈናቀል የዳረጉ የሰላም እና ጸጥታ ችግሮች እልባት ሊሰጣቸው ይገባል።

11. በስምምነቱ መሠረት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ምንም ዓይነት መድልዎ ሳይደረግባቸው ያላቸውን መብቶች ለማክበር፣ ለማስከበር እና ለማሟላት መንግሥት ቀዳሚ ኃላፊነት ሲሆን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሲፈናቀሉ ትተውት የሄዱትን የግል እና የጋራ ንብረታቸውን የመጠበቅ ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው እንዲመለሱ ለተደረጉ ተፈናቃዮች በመፈናቀል ወቅት ጥለውት የሄዱት ንብረትና ይዞታ በተቻለ መጠን እንዲመለስላቸው ካልሆነም ምትክ እንዲሰጣቸው እርምጃ የመውሰድ ግዴታ ያካትታል።

12. በተ.መ.ድ. መሠረታዊ መርሖዎች የዘላቂ መፍትሔ አማራጮች አተገባበር ላይ አጠቃላይ መመሪያ ለመስጠት ያለመው የበይነ-ኤጀንሲዎች ቋሚ ኮሚቴ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔዎች ማዕቀፍ (Inter-Agency Standing Committee Framework on Durable Solutions for Internally Displaced Persons) የዘላቂ መፍትሔ እርምጃዎችን ስኬት ለመመዘን ተያያዥነት ያላቸው 8 መስፈርቶችን ያስቀምጣል።[1] በሌላ በኩል ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሔዎችን ለመፈለግ መንግሥት ከተ.መ.ድ. እንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተቋማት ጋር በጋራ ያዘጋጀው የኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሔዎች ኢንሼቲቭ (Ethiopia Durable Solutions Initiative) የዘላቂ መፍትሔ አተገባበር ሂደት 8 መርሖዎችን መሠረት ሊያደርግ እንደሚገባ ያስቀምጣል። በዚህም መሠረት አንድ የዘላቂ መፍትሔ አማራጭ በተፈናቃዮች ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ፣ ደኅንነትና ክብርን የጠበቀ፣ መንግሥት የሚመራው እና የሚያስተባብረው፣ ተፈናቃዮችን እንዲሁም ተቀባይ ማኅበረሰብን ያሳተፈ፣ የተቀባይ ማኅበረሰብን ፍላጎት እንዲሁም አካባቢያዊ ሁኔታዎችን መሠረት ያደረገ፣ ተፈናቃዮች እስኪቋቋሙ ድረስ ምግብና ሌሎች መሠረታዊ አቅርቦቶች ሊቀርቡላቸው የሚገባ መሆኑን ያገናዘበ፣ ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና ትብብር የሚሳተፉበት፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ ተፈናቃዮችን በተለይም የሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ ወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋዊያንን እኩል ተሳትፎ እና መብት ያከበረ፣ እንዲሁም ዘላቂ እና ተፈናቃዮች እንደማንኛውም የሀገሪቱ ዜጎች ያለመድልዎ የሚተገበሩ መብቶች ያሏቸው መሆኑን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል።

[1] The IASC Framework on Durable Solutions for IDPs provides the below 8 criteria: safety and security, adequate standard of living, access to livelihoods, restoration of housing, land and property, access to documentation, family reunification, participation in public affairs, and access to effective remedies and justice.

የክትትሉ ዋና ዋና ግኝቶች

ሀ) በተፈናቃዮች ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑ

13. ኢሰመኮ የካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም. በትግራይ ክልል የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ የተከናወነ የክትትል ሪፖርት ይፋ አድርጎ የነበረ ሲሆን፣ በወቅቱ በተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይገኙ የነበሩ አብዛኛዎቹ ሰዎች ወደ ቀድሞ አካባቢያቸው መመለስ የመጀመሪያ ምርጫቸው መሆኑን ለኢሰመኮ ማስረዳታቸው ተገልጾ ነበር።

14. ወደ አላማጣ፣ ኮረም፣ አፍላ፣ ራያ አላማጣ፣ ጨርጨር እና ዛታ አካባቢዎች እንዲመለሱ የተደረጉ ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ተፈናቃዮች በራሳቸው ፍላጎት የተመለሱ መሆናቸውን እንዲሁም በሚመለሱበት ወቅት የሕዝብ መጓጓዣ አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች ተመድበው ወደየአካባቢዎቻቸው እንዳደረሷቸው ገልጸዋል። በተመሳሳይ ወደ ጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ እንዲመለሱ የተደረጉ ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ተፈናቃዮች የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር የጸጥታ ሁኔታውን አስጠብቆ ወደ ቀያቸው እንዲመልሳቸው ግፊት ሲያደርጉ እንደነበረ እና የመመለስ ሂደቱም በዚሁ መሠረት ፈቃደኝነታቸውን ባከበረ መልኩ የተከናወነ መሆኑን አስረድተዋል።

ለ) የተፈናቃዮችን ደኅንነትና ክብርን የጠበቀ ስለመሆኑ

15. በአላማጣ፣ ኮረም፣ አፍላ፣ ራያ አላማጣ፣ ጨርጨር እና ዛታ አካባቢዎች ከሚያዝያ 7 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ የመከላከያ ሰራዊት እና የፌዴራል ፖሊስ አባላት የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ እያስጠበቁ የሚገኙ ቢሆንም ወደ እነዚህ አካባቢዎች እንዲመለሱ የተደረጉ ተፈናቃዮች የደኅንነት ሥጋት ያለባቸው መሆኑን ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

16. በክትትሉ ወቅት በራያ አላማጣ ወረዳ ዋጃ ጡመጋ ቀበሌ በጤና ጣቢያ ውስጥ የሚገኙ ተመላሾች ከሚገኙበት በቅርብ ርቀት ላይ የታጠቁ ኃይሎች የነበሩ በመሆኑ፤ እንዲሁም በአላማጣ ከተማ 02 እና 03 ቀበሌ በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲቆዩ የተደረጉ ተመላሾች ትጥቅ ሳያስረክቡ ማኅበረሰቡን የተቀላቀሉ ታጣቂዎች የነበሩ በመሆኑ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ለመኖር እንዳልቻሉ ለኢሰመኮ አስረድተዋል። ተመላሾች ከትምህርት ቤቶቹ ግቢ ውጭ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ጥቃት የሚደርሱባቸው መሆኑን ገልጸው፤ “እንደእስረኛ ታፍነን ለመኖር ተገደናል” በማለት ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

17. ወደ ጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ አካባቢዎች ተፈናቃዮችን የመመለስ ሥራ ሲጀመር የተፈናቃዮች ከየት አካባቢ የተፈናቀሉ መሆኑን የተደራጀ መረጃ ባለመኖሩ ከጸለምት አካባቢ የተፈናቀሉ ሰዎችን ከሌላ አካባቢ ከተፈናቀሉ ለመለየት ተፈናቃዮች ከተፈናቀሉባቸው አካባቢዎች በመጡ የሀገር ሽማግሌ ተወካዮች እየተለዩ እንዲጓዙ ተደርጓል። ይህ የልየታ መንገድ በተፈናቃዮች ላይ ቅሬታ መፍጠሩን እና በውይይት እንዲፈታ ተደርጎ ተፈናቃዮች ቀስ በቀስ እንዲመለሱ የተደረገ መሆኑን ኢሰመኮ ተረድቷል። ተመላሾች በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ ሲገልጹ፦

"ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ.ም. ትሄዳላችሁ ተብለን ተዘጋጅተን እያለ ከጸለምት አካባቢ ተወክለው የመጡ የሀገር ሽማግሌዎች የሚሄድ እና የማይሄድ ሰው መምረጥ ጀመሩ። ይሄም የመመለስ ሂደቱን በመራጮቹ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አድርጎት ነበር። የተወሰኑ ተፈናቃዮች ወደ መኪና ከተሳፈሩ በኃላ እንደገና እንዲወርዱ ተደርጓል። በዚህም ምክንያት ጉዞው ለአንድ ቀን ተራዝሞ ነበር። ጉዞ ከጀመርን በኃላም ቢሆን መንገድ ላይ የማጉላላት ሁኔታም ነበር" ብለዋል።

18. በመጀመሪያው ዙር የተመለሱ የላዕላይ ጸለምት አካባቢ ተፈናቃዮች የተመለሱት የመጀመሪያ ቀን ምግብ ሳይቀርብላቸው በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲያድሩ ከተደረገ በኋላ በሁለተኛው ቀን ወደ ቤተሰቦቻቸው እና ቤታቸው እንዲገቡ መደረጉን ተመላሾቹ ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

19. በክትትሉ በተሸፈኑ ሁሉም አካባቢዎች መደበኛ የአስተዳደር መዋቅር ባለመኖሩ የሰላምና ጸጥታ የማስከበር ሥራ እየሠራ የሚገኘው የመከላከያ ሰራዊት መሆኑን ኢሰመኮ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ተመላሾች እና ከትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ኃላፊዎች ለመረዳት ችሏል።

20. በጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ በተመላሾች እና በአካባቢው ማኅበረሰብ መካከል ያለው ግንኙነት ሰላማዊ ቢሆንም ጦርነቱን ተከትሎ በአማራ ክልል በኩል አካባቢውን ሲያስተዳድሩ በነበሩ አካላት እና ወደ አካባቢው በተመለሱ የትግራይ ክልል የፖለቲካ መራሮችና የጸጥታ አካላት መካከል መፍትሔ ያላገኙ አለመግባባቶች አሉ። ይህም በተመላሾች ደኅንነት ላይ ሥጋት ማሳደሩን፤ መኖሪያ ቤታቸው ተለይቶ ድንጋይ የሚወረወርባቸው እንዲሁም ድብደባ የሚፈጸመባቸው ተመላሾች መኖራቸውን፤ በዚህም ምክንያት ለዳግም መፈናቀል የተዳረጉ ተመላሾችን እና ተጎጂዎችን ጭምር በማነጋገር ኢሰመኮ ለማረጋገጥ ችሏል።

21. በክትትሉ በተሸፈኑ ሁሉም አካባቢዎች በተመላሾች እና በተቀባይ ማኅበረሰብ መካከል ግጭት ባይኖርም በመፈናቀል ወቅት የተፈጠረ ቂምና ቁሩሾ በዕርቅ እና በውይይት የሚፈታበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ በተመላሾች ደኅንነት ላይ ሥጋት ማሳደሩን ኢሰመኮ በክትትሉ ለመረዳት ችሏል።

ሐ) ተፈናቃዮች እስከቋቋሙ ድረስ የሚቀርበውን ምግብ እና መሠረታዊ አቅርቦቶች በተመለከተ

22. ከመፈናቀላቸው በፊት በተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ይሠሩ የነበሩ ተመላሾች አብዛኛዎቹ ወደ ሥራቸው ያልተመለሱ ሲሆን፤ የመንግሥት ሠራተኞችም ሆኑ በንግድና እርሻ ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ ተመላሾች በሌሎች ሥራዎች ተሰማርተው ኑሯቸውን ለመምራት ቢፈልጉም በጸጥታ ችግር ተንቀሳቅሶ ለመሥራት አለመቻላቸውንና በዚህም የተነሳ ለችግር መዳረጋቸውን ለኢሰመኮ አስረድተዋል። እንዲሁም ተመላሾች ይህ ክትትል እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ምግብ እና ሌሎች መሠረታዊ አቅርቦቶችን ያላገኙ በመሆኑን ለከፋችግር በተለይም ለረሀብ መጋለጣቸው ኢሰመኮ በክትትሉ ወቅት በጊዜያዊ ማቆያዎች ባደረገው ምልከታ ለማረጋገጥ ችሏል።

23. በጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ አካባቢዎች ለተመለሱ ለተወሰኑ ተፈናቃዮች በሚመለሱበት ወቅት በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር በኩል የ1500 ብር የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው መሆኑን ኢሰመኮ ከተመላሾች ለመረዳት ችሏል።

24. ኢሰመኮ ኅዳር 20 ቀን 2017 ዓ.ም. በመቐለ ከተማ ባካሄደው የምክክር መድረክ ላይ የተገኙ የሰሜን ምዕራብ እና ደቡባዊ ዞን የሥራ ኃላፊዎች፦ ማይፀብሪ፣ አላማጣ እና ራያ አላማጣ ለተመለሱ ተፈናቃዮች በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በተወሰነ መልኩ ምግብ መቅረብ የጀመረ ቢሆንም በተቀሩት አካባቢዎች ግን ምንም ዐይነት ምግብና መሠረታዊ አገልግሎቶች ባለመቅረቡ ተመላሾች ለዳግም መፈናቀል እና ለተለያዩ ችግሮች መዳረጋቸውን ገልጸዋል።

25. በተለይም በአሁኑ ወቅት ሰሜን ምዕራብ ዞን ጸለምት፣ ላዕላይ ጸለምት እና ማይፀብሪ ከተማ የሚገኙ ከ56 ሺ በላይ ተመላሾች በምግብ አቅርቦት መቋረጥ ምክንያት ለከፋ ችግር ተዳርገው የሚገኙ መሆኑን ኢሰመኮ ተመላሾችን እንዲሁም የሰሜን ምዕራብ ዞን የሥራ ኃላፊዎችን በስልክ በማነጋገር ለመረዳት ችሏል።

መ) ማኅበራዊ አገልግሎት እና መሠረተ ልማትን በተመለከተ

26. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዲመለሱ በሚደረጉባቸው አካባቢዎች በጦርነት የወደሙ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች አስፈላጊ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እና መሠረተ ልማቶች መሟላታቸው እና አገልግሎት ለመስጠት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት:: በክትትሉ በተሸፈኑ አካባቢዎች እንዲመለሱ የተደረጉ ተፈናቃዮች በጦርነቱ ወቅት አብዛኛዎቹ የጤና ተቋማት የወደሙ እና የሕክምና መሣሪያዎች የተዘረፉ በመሆኑ አገልግሎት ለማግኘት መቸገራቸውን ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

27. ኢሰመኮ ለምሳሌ በአላማጣ ሆስፒታል የመስክ ምልከታ ያደረገ ሲሆን ሆስፒታሉ ከድንገተኛ ሕክምና እና የወሊድ አገልግሎት ውጭ ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት ያልጀመረ መሆኑን ለመረዳት ችሏል። ሆስፒታሉ ላለፉት 5 ዓመታት በጀት ያልተመደበለት እና በባንክ የነበረው ተቀማጭ ሒሳብ የታገደበት በመሆኑ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለማሟላት ተቸግሯል። ለምሳሌ የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ግዥ መፈጸም ባለመቻሉ እናቶች ለወሊድ በሚመጡበት ወቅት ፈሳሽ እና የዱቄት ሳሙና ይዘው እንዲመጡ የሚጠየቁ መሆኑን ኢሰመኮ ተመልክቷል።

28. በጦርነቱ ወቅት ትምህርት ቤቶች የወደሙ እና በከፊል የፈረሱ በመሆኑ በራያ አላማጣ እና ዛታ ከጦርነቱ በኋላ በአብዛኛው የትምህርት አገልግሎት ያልተጀመረ ሲሆን፣ በተለይም በአላማጣ፣ ኮረም፣ አፍላ እና ጨርጨር ከ2016 ዓ.ም. ጀምሮ በከፊል ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን ኢሰመኮ ከወረዳዎቹ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት ችሏል።

29. በተመሳሳይ በሰሜን ምዕራብ ዞን አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች በጦርነቱ የወደሙና የተዘረፉ በመሆናቸው እንዲሁም በአካባቢው የሲቪል አስተዳደር ባለመኖሩ ትምህርት

የሚሰጥበትን ቋንቋ አስመልክቶ ውሳኔ ባለመሰጠቱ ትምህርት ያልተጀመረ መሆኑን ኢሰመኮ ለመረዳት ችሏል።

30. ኢሰመኮ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ካከናወነው ክትትል በኋላ ተመላሾች አሁን ላይ የሚገኙበትን ሁኔታ ለመረዳት የደቡባዊን ዞን እና ሰሜን ምዕራብ ዞን ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በስልክ ያነጋገረ ሲሆን ይህ ሪፖርት ይፋ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ተመላሾች በሚገኙባቸው አካባቢዎች አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ጥቂት የጤና ተቋማት ቢኖሩም የባለሙያዎች እጥረት ፣ የመድሃኒት አቅርቦትና የሕክምና መሳሪያ ባለመኖሩ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት መቸገራቸውን እንዲሁም የሕክምና ድጋፍ የሚያደርጉ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች ለተመላሾች ድጋፍ ለማድረግ መቸገራቸውን ገልጸዋል።

31. በተመሳሳይ የትምህርት ሁኔታንም በተመለከተ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች በራያ አላማጣ ወረዳ በጸጥታ ችግር እንዲሁም በጦርነቱ ወቅት ያልተከፈለ የ17 ወር የመምህራን ደመወዝ እስካሁን ባለመከፈሉ ከዚህ ቀደም ከተዘጉ 15 ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ ሌሎች 7 ትምህርት ቤቶች ትምህርት መስጠት ማቆማቸውንና በተመሳሳይ በአላማጣ ከተማም 3 ትምህርት ቤቶች የተዘጉ መሆኑን ኢሰመኮ ከኃላፊዎቹ ለመረዳት ችሏል።

32. በክትትሉ በተሸፈኑ አካባቢዎች ከጦርነቱ በኋላ የሲቪል አስተዳደር መዋቅር ባለመኖሩ ተመላሾች የቀበሌ መታወቂያን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ ይህም ማኅበረሰቡ መደበኛ የመንግሥት አገልግሎቶችን እንዳያገኝ ከማድረጉም ባሻገር ዓለም አቀፍ የሰብአዊ ድጋፍ ድርጅቶች ለተመላሾች ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ እንቅፋት እንደሆነባቸው ከድርጅቶቹ ተወካዮች ለመረዳት ተችሏል።

ሠ) ቤት፣ መሬት እና ሌሎች ንብረቶችን መልሶ የማግኘት መብት

33. በደቡባዊ ዞን ሥር ወደሚገኙ አካባቢዎች እንዲመለሱ ከተደረጉ ተፈናቃዮች አብዛኛዎቹ በጦርነቱ ወቅት ቤቶቻቸው እና ሌሎች የግል ንብረቶቻቸው የወደሙባቸው እና የተዘረፉባቸው በመሆኑ በጤና ጣቢያ እና በትምህርት ቤቶች ግቢ ውስጥ እንዲሁም በዘመድ ቤት ተጠግተው ለመኖር መገደዳቸውን አስረድተዋል። በተለይም በአላማጣ ከተማ ከመፈናቀላቸው በፊት በቀበሌ ቤቶች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ወደአካባቢያቸው ሲመለሱ የቀበሌ ቤቶቹ ለሌሎች ሰዎች ተላለልፈው እንደጠበቋቸው፤ በተመሳሳይ የሌሎች ተመላሾች የግል መኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ቦታዎች በሌሎች ሰዎች ተይዘው የሚገኙ መሆኑን ተመላሾች ገልጸዋል።

34. በራያ አላማጣ ወረዳ ዋጃ ጡሙጋ ቀበሌ ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ተመላሾች የእርሻ መሬታቸው ከሌሎች አካባቢዎች በመጡ ሰዎች መያዙን ገልጸው አቤቱታቸውን የሚያቀርቡበት የፍትሕ አካል ባለመኖሩ ለጉዳዩ ሕጋዊ መፍትሔ ለማግኘት እንደተቸገሩ ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

35. ወደ ሰሜን ምዕራብ ትግራይ እንዲመለሱ የተደረጉ ተፈናቃዮች አብዛኛዎቹ ወደ ቤታቸው ተመልሰው መግባት የቻሉ ቢሆንም የቤት ዕቃዎቻቸው የተዘረፉ በመሆኑ ሲመለሱ ቤታቻው ባዶ ሆኖ የጠበቃቸው መሆኑን ገልጸዋል። በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ 1 ተመላሽ “እኔ ስመለስ ቤቴ ባዶ ሆኖ ነው የጠበቀኝ። ለንግድ

ስጠቀምባቸው የነበሩ ፍሪጅ፣ ወንበሮች፣ ጀኔራተር እና ሌሎች ዕቃዎች ተዘርፈዋል" በማለት ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

36. ይህ ክትትል እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ በክትትሉ በተሸፈኑ አካባቢዎች የተመለሱ ተፈናቃዮችን መልሶ የማቋቋም ሥራ ያልተጀመረ ሲሆን፣ ነገር ግን በትግራይ ክልል ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ የዘላቂ መፍትሔ ዕቅድ የተዘጋጀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ረ) ፋትሕ የማግኘት መብት

37. በክትትሉ በተሸፈኑ አካባቢዎች የፍትሕ ተቋማት ማለትም ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤቶች እና ፍርድ ቤቶች ወደ ሥራ ያልገቡ በመሆናቸው ተመላሾች በመፈናቀል ወቅት ለደረሰባቸው የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ፍትሕ የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ ካለመኖሩ በተጨማሪ ለተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች የሚጋለጡ መሆኑን ኢሰመኮ በክትትሉ ለማወቅ ችሏል።

ምክረ ሐሳቦች

38. **ኢሰመኮ የክትትሉን ግኝቶች መሠረት በማድረግ ለፌደራል መንግሥት የሚከተሉትን ምክረ ሐሳቦች ያቀርባል፦**

- ተመላሾች ደኅንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ ወደ ቀድሞ ኑሯቸው ተመልሰው መኖር እንዲችሉ አስቻይ ሁኔታዎችን ሊያመቻች እና በዘላቂነት እስኪቋቋሙ ድረስ በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ተደራሽ ምግብ እና ሰብአዊ ድጋፎች እንዲቀርብ፤
- ተመላሾች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ደኅንነታቸው በተሟላ ሁኔታ ተጠብቆ በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ የተመላሾችን ደኅንነት የሚያረጋግጡ የጸጥታ አካላት እንዲመደቡ እንዲሁም የማኅበረሰባዊ ውይይት የሚያጠናክሩ እርምጃዎች እንዲተገብሩ፤
- ተመላሾች መደበኛ የመንግሥት አገልግሎቶችን ጨምሮ የጤና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች በተሻለ ሁኔታ እንዲያገኙ ለማድረግ ጉዳት የደረሰባቸውን ተቋማት መልሶ በማቋቋም፣ የሲቪል አስተዳደር መዋቅርን በመዘርጋት እንዲሁም አስፈላጊ ግብዓቶችን እና የሰው ኃይልን በማሟላት በአፋጣኝ የተሟላ አገልግሎት ለማስጀመር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን እንዲመቻቹ፤
- ተመላሾች ትተዋቸው የሄዷቸውን ቤት እና ሌሎች ንብረቶች መልሰው የሚያገኙበትን እንዲሁም የሕግና ፍትሕ ዋስትና የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሕግ አስከባሪ እና የፍትሕ ተቋማት አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ እንዲደረግ እንዲሁም ሌሎች በዚህ የክትትል ሪፖርት የተለዩ ክፍተቶችን ምላሽ ለመስጠት መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማስተባበር እንዲሠሩ እና በቀጣይ የሚከናወኑ ተፈናቃዮችን ወደቀድሞ ቀያቸው የመመለስ ሂደቶች የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶችን መሠረት ያደረጉ እና ያሟሉ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል።

. . .

ስለ ኢሰመኮ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ መሠረት ነጻ ፌዴራላዊ መንግሥት አካል ሆኖ የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። *(የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/14 እና አዋጅ ቁጥር 210/1992 በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው)*